የሆቴልና የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል
Catering and Tourism Center

**ዜና መጽሔት**

**Business Name**

**ቅጽ 2 ቁጥር 4**

# ሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተካሄደ

**በህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳሬክቶሬት የተዘጋጀ**

**ጥቅምት 2012**



ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ ጥቅምት 1 እና 02/2012

ላለፉት 50 ዓመታት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችን በማፍራት አንጋፋ ተቋም የሆነው የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የ2012 ዓ.ም ዕቅዱን ለባለድርሻ አካላት አቅርቦ ውይይት ተካሂዷል።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የኢንስቲትዩቱን ተማሪዎች ቀጣሪ በሆኑ ተቋማት ላይ ጥናት በማስደረግ ውጤታማ መሆናቸውን ገልፀዋል።

ኢንስቲትዩቱ በሚመደብለት በጀት የሚሰራውንም ስራ የባለድርሻ አካላት ፍላጎት የተካተተበት እንዲሆን መድረኩ መዘጋጀቱን ዋና ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

የኢንስቲትዩቱን የ2012 በጀት ዓመት ዕቅድ አቶ ተመስገን በቀለ ካቀረቡ በኋላ ውይይት ተካሂዶበታል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በሀገራችን እየታየ ያለው ስራ ለዘርፉ ተስፋ የሚሰጥ ነው። የአንድነት ፓርክ መከፈትና የሸገር የወንዝ ዳርቻ ልማት መጀመር ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ትልቅ እርምጃ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

አንጋፋው ተቋም ራሱን በአዲስ የምዕራፍ ለማስጓዝ አቅዶ እየሰራ መሆኑን የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ገልፀዋል።

ተቋሙን የልህቀት ማዕከል ለማድረግ ቱሪዝም ዲፓርትመንት ካላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመነጋገር በጋራ ለመስራት መታቀዱን አቶ ገዛኸኝ ተናግረዋል።

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከ50 ዓመታት በላይ በብቸኝነት የዘርፉን ባለሙያዎች ሲያፈራ የቆየ አንጋፋ ተቋም በመሆኑ የዕድሜውን ያህል አለማደጉ የሚያስቆጭ እንደሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ።

ዛሬ ለሚከፈቱ ዩኒቨርስቲዎች የልምድ መቀመሪያ መሆን የሚገባው ተቋም በዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ በመደበኛው መርሃግብር መስጠት አለመቻሉ ኢንስቲትዩቱ ምን ያህል መዘንጋቱን ማሳያ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ቱሪዝም ላይ እየሰሩ ያሉትን ሥራ በሚመጥን ደረጃ በዘርፉ የተሰማራን አካላት አብረን መራመድ ይገባናል ብለዋል።

ኢንስቲትዩት የማይተካውን የሰው ኃይል በዘርፉ የሚያመርት በመሆኑ ብቃት ያለው ባለሙያ ማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት ተጠቁሟል።

ኢንስቲትዩቱ ስልጠናውን የሚሰጠው በገነት ሆቴል ነው። ይህ ሆቴል ዛሬ የሰው ሀይል ከሚፈልጉት ሆቴሎች ደረጃ ጋር የሚቀራረብ ባለመሆኑ ደረጃውን የጠበቀ ማስተማሪያ ሆቴል ሊኖረውና ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ሊያፈራ ይገባል።

አሁን የኢንስቲትዩቱ አመራሮች ቁጭት አድሮባቸው ለውጥ ለማምጣት ፍላጎቱ ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነቱም ያላቸው ናቸው።

የሚያግዛቸው ህጎች በወቅቱ ፀድቀው ወደ ተግባር ሊገቡላቸው ይገባል።

በአዳማ ከተማ በተካሄደ የውይይት መድረክ የ2012 በጀት ዓመት የ3 ወር ዕቅድ አፈፃፀም ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል።



Caption describing picture or graphic.

“To catch the reader's attention, place an interesting sentence or quote from the story here.”



Caption describing picture or graphic.

## ኢንስቲትዩቱ 12ኛውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን ተከበረ

ጥቅምት 04/2012 ዓ.ም የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት 12ኛውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን በዛሬው እለት ኢንስቲትዩቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በደማቅ ሁኔታ አከበረ፡፡ በበዓሉ አካባበር ላይ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ፣ የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞችና ሰልጣኞች ተገኝተዋል፡፡ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በየዓመቱ በተለያዩ መሪ ቃሎች ሲከበር የቆየ ሲሆን፤ በዚህ ዓመትም “ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሀነታችን ድምር ውጤትና የአንድነታችን ምሰሶ ነው” በሚል መሪ ቃል ተከብሯል።



## አዲስ ሰልጣኞች ትውውቅ ተካሄደ





**ጥቅምት 27/28 /2012 ዓ.ም**

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከዘጠኙ ክልሎችና ከሁለት ከተማ አስተዳደር በሆቴልና ቱሪዝም ስልጠና ለመውሰድ ፍላጎት ከነበራቸው ሰልጣኞች መስፈርቱን ያሟሉ ከ500 በላይ የቀን መርሃ ግብር ሰልጣኞች የተቋም ትውውቅ አካሄደ።

በትውውቅ ፕሮግራሙ የተቋሙ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ዘንድሮ የተቀበልናቸው ሰልጣኞች በተቋሙ ታሪክ 51ኛ መሆናቸውንና የሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪ 50 ዓመታትን በብቃት ያሰለጠነ ለሌሎች መሰል ተቋማት መፈጠር የበኩሉን አስተዋጽኦ ወደ አበረከተው አንጋፋ ተቋም እንኳን ደህና መጣችሁ ብለዋል።







ምላሽ ቢሰጥም በቂ አይደለም ያሉት በወር የሚከፈለው የኪስ ገንዘብ ዝቅተኛ መሆንና የደንብ ልብሰ ለማሰፋት ካለው ኑሮ ውድነት ጋር ከፍተኛ ችግር መሆኑን ሰልጣኞች ተናግረዋል። ይህን የገለፁት ከተለያየ ክልል መጥተው አዲስ አበባ ውስጥ ቤት ተከራይቶ፣ ምግብ በልቶ ለመኖር እና የትምህርት ቁሳቁስን ለማሟላት 510 ብር በቂ ነው ብለን ስለማናምን ቢያንስ ዶርም እንኳ ማግኘት ቢቻል የሚል አስተያታቸውን ሰጥተዋል።

የሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪ የሚፈልገውን ሙያዊ ስነምግባር አሟልታችሁ እንደቀደምት የተቋሙ ሰልጣኞች መልካም ስም ያተረፋችሁ እንድትሆኑ ከወዲሁ መዘጋጀት ይጠበቅባችኋል ካሉ በኋላ ሰልጣኞች በሁሉም ዘርፍ በርትቶ በመማርና በሚያጋጥሙ ችግሮች ሳይደናቀፉ ስኬታማ ባለሙያ ለመሆን መትጋት እንዳለባቸው በመግለጽ የግቢ ቆይታቸው መልካም እንዲሆንላቸው ተመኝተዋል። የተቋሙ አካዳሚክና ምርምር ዲን አቶ ግሩም ግርማ በበኩላቸው የዘንድሮ የተማሪ ቅበላ ከሌሎች ዓመታት ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ የጨመረና መንግስት አዲስ በተቀረጸው ሥርዓተ ትምህርት የሚማሩ መሆናቸው እድለኞች መሆናቸውን ገልጸዋል። የቱሪዝም ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ በቀለ ኡማ ከሰልጣኞች ስለሚጠበቀው ተግባርና ኃላፊነት ሰነድ ያቀረቡ ሲሆን በሰነዱ መነሻነት ከሰልጣኞች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ከትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ከአካዳሚክ ዲን ምላሽ ተሰጥቶበታል። ምላሽ ቢሰጥም በቂ አይደለም ያሉት በወር የሚከፈለው የኪስ ገንዘብ ዝቅተኛ መሆንና የደንብ ልብሰ ለማሰፋት ካለው ኑሮ ውድነት ጋር ከፍተኛ ችግር መሆኑን ሰልጣኞች ተናግረዋል። ይህን የገለፁት ከተለያየ ክልል መጥተው አዲስ አበባ ውስጥ ቤት ተከራይቶ፣ ምግብ በልቶ ለመኖር እና የትምህርት ቁሳቁስን ለማሟላት 510 ብር በቂ ነው ብለን ስለማናምን ቢያንስ ዶርም እንኳ ማግኘት ቢቻል የሚል አስተያታቸውን ሰጥተዋል።

**‹‹ የሆስፒታሊቲ ኢንደስትሪ የሚፈልገውን ሙያዊ ስነምግባር አሟልታችሁ እንደቀደምት የተቋሙ ሰልጣኞች መልካም ስም ያተረፋችሁ እንድትሆኑ ከወዲሁ መዘጋጀት ይጠበቅባችኋል››**

# List of World Heritage Sites in Ethiopia

| Image | Location | Area | UNESCO | Description | |
|---|---|---|---|---|---|
| Aksum |  | Tigray Region 14°7′48.684″N 38°43′6.996″E | — | 15; 1980; i, iv | The ruins of the city of Aksum, dating from the 1st to the 13th century, mark the heart of an- |
| Fasil Ghebbi |  | Amhara Region 12°36′24.912″N 37°27′58.212″E | — | 19; 1979; ii, iii | The fortress was the residence of the Ethiopian emperors during the 16th and |
| Harar Jugol, the Fortified Historic Town |  | Harari Region 9°18′32″N 42°8′16″E | 48 (120) | 1189; 2006; iv, v | The city is on a plateau and surrounded by gorges and sa- |
| Konso Cultural Landscape |  | Southern Nations, Nationalities, and People's | 14,000 (35,000) | 1333; 2011; iii, v | The site features 55 kilometres (34 mi) of stone- |
| Lower Valley of the Awash |  | Afar Region 11°6′0.216″ | — | 10; 1980; ii, iii, iv | Palaentological findings from at least four million |
| Lower Valley of the Omo |  | Southern Nations, Nationalities, and People's | — | 17; 1980; iii, iv | The prehistoric site near Lake Turkana is the |
| Rock-Hewn Churches, Lalibela |  | Amhara Region 12°1′45.66″N 39°2′25.512″E | — | 1978\|18; 1978; i, ii, iii]} | The site contains twelve medieval rock hewn churches from |
| Simien National Park † |  | Amhara Region 13°11′0″N 38°4′0″E | 22,000 (54,000) | 9; 1978; vii, x | The eroded Ethiopian plateau comprises |
| Tiya |  | Southern Nations, Nationalities, and People's | — | 12; 1980; i, iv | The archaeological site contains 36 monu- |

**Tentative list[**

IBale Mountains National Park (2008)

Dirre Sheik Hussein Religious, Cultural and Historical Site (2011)

Holqa Sof Omar: Natural and Cultural Heritage (Sof Omar: Caves of Mystery) (2011)

Gedeo Mixed Cultural and Natural Landscape (2012)

Melka Kunture and Bachilt Archaeological Site (2012)